# ደህንነቱ የተጠበቀ ቤተሰብ። ደህንነቷ የተጠበቀ ዓለም።

ዕድሜያቸው ከ 0-12 ዓመት በሆነ ሕጻናይ ላይ የሚያጋጥም ወሲባዊ በደል መከላከል የሚመለከት መረጃ ጽሑፍ ለወላጆች እና ኣሳዳጊዎች

ይህ ጽሑፍ ለወላጆች፣ ሞግዚቶች እና ሌሎች ህጻናት የሚንከባከቡ ሰዎች ህጻናት ላይ ሊወርድ የሚችል ወሲባዊ በደል ለመከላከል እንዲረዳቸው ታስቦ የተዘጋጀ ነው። የኣንዳንድ ወላጆች ኃይለኛ ፍራቻ ልጆቻቸው እንዳይጎዱ ወይም እንዳይበደሉ ነው። እኛ ሁልግዜ ሌሎች ሰዎች ልጆቻችንን እንዴት ይይዟቸዋል/ይንከባከቧቸዋል መቆጣጠር ኣንችልም፤ ልጆቻችንም ቢሆኑ ሌሎች እንዴት ይንከባከቧቸዋል መቆጣጠር ኣይችሉም። ሆኖም ግን ጥሩ ነገር ሁልግዜ እኛ የራሳችንን ባህሪያት መቆጣጠር እንችላለን። ልጆቻችንንም ኣርኣያችንን እንዲከተሉ እንዲያደርጉ ማስተማር እንችላለን። ወላጃ ወይም ኣሳዳጊ እንደመሆንዎ መጠን ልጆቻችሁን ሌሎች እንዴት ሊይዟቸው እንደሚችሉ እና እነሱም እንዴት ሌሎችን መያዝ እንዳለባቸው ማስተማር የሚችሉት የቅርብ ሰው እርስዎ ኖት። ሁሌም የናንተን ኣርኣያነት ስለሚከተሉ!

እዚህ ጽሑፍ ውስጥ ስለ ወሲባዊ በደል እና ደህንነት ከልጆቻችሁ ጋር እንዴት መወያየት እንዳለባቹሁ ሃሳብ ታገኛላችሁ። እንደዚህ ያሉ ውይይቶች ከልጃቻሁ ጋር ያላችሁን መቀራረብ የጠብቃሉ ብሎም በደልን ለመከላከል ያግዛሉ። ምንም እንኳን ወላጆች ስለዚህ ጉዳይ ከልጆቻቸው ጋር ቢወያዩበትም ኣንዳንድ ግዜ ልጆች ወሲባዊ በደል ሊደርስባቸው ይችላል። ይህ ጽሑፍ በተጨማሪ ይህ ጉዳይ ሲያጋጥም ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ይጠቁማል።

ደህንነቱ የተጠበቀ ቤተሰብ እና ደህንነቷ የተጠበቀ ዓለም መፍጠር ላይ ሁላችንም ተራ ኣለን። እባካችሁ እርዳታ ከፈለጋችሁ ኣነጋግሩን።
ከናንተ ጋር ለመነጋገ ሁሌም ደስተኞች ነን።
የሃርቨርቪው ሴንተር ፎር ሴክሹዋል ኣሷልት ኤንድ ትራውማቲክ ስትረስ ቴሌፎን


በኢንተኔት፡
www.hcsats.org
206-744-1600


## ስለ ጤንነቱ የጠበቀ ጾታዊ ዝምድና...

▶ ልጆቻችሁን **የሰውነት ክፍል ትክክለኛ ስያሜ** ሃፍረተ ኣካላታቸውን ጨምሮ ማስተማር ጠቃሚ ነው። እንዲዚህ ኣድርጎ እነዚህን ቃላት በማስተማር፣ እነዚህን ስያሜዎች መጠቀም ምንም እንዳልሆነ እንዲያውቁ እና የሆነ የሰውነት ኣካላቸውን ችግር ሲያጋጥማቸው በግልጽ እንዲነግሯችሁ ያግዛል።

▶ **የተወሰኑ የሰውነት ክፍሎቻቸው ሓፍረታቸው** (የግላቸው እንደሆኑ) እንደሆኑ ኣስተምሯቸው። እነዚህ ሕፍረተ ኣካላት የሚባሉት ሁሌም በመዋኛ ልብስ የምንሸፍናቸው የሰውነታችን ኣካላት ናቸው።

▶ ህጻናት ሁሌም ልጆች ከየት እንደሚመጡ፣ እንዴት እንደሚያድጉ፣ ራስን ችሎ መጸዳዳት፣ የሰውነት ክፍሎች እና የስውነታቸውን ጽዳት እንዴት ሁሌም እንድሚጠብቁ በተደጋጋሚ ይጠይቃሉ። **እነዚህ ጥያቄዎች እንዲመለሱላቸው ይፈልጋሉ**። ለነዚህ ጥያቄዎች እንዴት ኣድርገው ቀጥተኛ እና ከልጆቹ እድሜ ጋር የሚስማማ ተገቢ መልስ መቼ እንደሚሰጡ ኣስቀድሞ ማሰብ እና ማወቅ ጥሩ ነገር ነው።

▶ ልጆች ስለነዚህ ነገሮች ለመወያየት ዝግጁ መሆናቸውን እንዴት ማወቅ ይችላሉ? **መጠየቅ ከጀመሩ ለመዘጋጀታቸው ጥሩ ምልክት ነው!** በዕድሜ ላነሱ ሕጻናት መሰረታዊ መረጃ መስጠት በቂ ነው። ተጨማሪ ጥያቄ ካላቸው ይጠብቁ። ሁል ግዜ እርስዎ የሚሉት ትክክለኛ እና ቀን መሆኑን ያረጋግጡ።

▶ ኣንዳንድ ግዜ በዕድሜ ባነሱ ልጆች ዘንድ **ጾታዊ ባህሪያት እና ጨዋታ** እንደ ቤተሰብ ቤተስብ እና ዶክተር ዶክተር የመሰሉ ጫዋታዎች የተለመዱ ናቸው። ልጆች የሰውነታቸውን ክፍል ለማወቅ መጣር እና መነካካት በዕድሜ ባነሱ ሕጻናት መሃከል የተለመደ ነው። የሚቀጥለው ክፍል ላይ እንደተገለጸው የት መንካት እንዳለባቸው እና እንደሌለባቸው ማስተማር እና ስርዓት ማውጣት ትችላላችሁ። ልጁ የሚያሳየው ጾታዊ ባህሪያት የተለመደ ወይም ያልተለመድ የሚያሳስብ መሆኑን ለማወቅ ወደ ማእከላችን መደወል ትችላላችሁ።

▶ ቤተሰቦች በጋራ ማንበብ የሚችሏቸው ስለ ስውነታችን ኣካላት፣ ሕጻናት እና ደህንነት የሚገልጹ **ጥሩ መጻሕፍት** ኣሉ። የመጻሕፍቱ ዝርዝር ለማግኘት ድሕረ ገጻችንን **www.hcsats.org** በመጎብኘት "Resources" የሚለውን ኣርእስት ይጫኑ።

"የያንዳንዱ ሰው ሰውነት ልዩ እና ኽቡር ነው።"

"ሰውነትህ ያራስህ ነው። ሰውነትህን መንከባከብ እና ሁሌም ጤነኛነቱን እና ጽዳቱን ጠበቅ ኣስፈላጊ ነው።"

"የጥያቄህን መልስ ኣላውቀውም ግን በመጠየቅህ ደስ ብሎኛል። ይህን ጉዳይ የሚመለከት መጽሓፍ ፈልጌ ካገኘሁ ቡኋላ በጋራ እያነበብን እንማራለን።"

"ልጆች የሚያድጉት በሴቶች/በእናቶች ማሕጸን ውስጥ ነው።"

"ሰውነትህን ማየት እና መንካት ምንም ኣይደለም። ይህን መኟታ ቤትህ ወይም መጸዳጃ ቤት ማድረግ ትችላለህ ።"

መፍቃድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለማሳየት ኣጋጣሚ ያመቻቹ። ይህ ልጆች ሰውነታቸው ላይ መቅረብ እንዴት መፍቀድ እና መከልከል እንደሚችሉ ወይም በጭራሽ ኣለመፈለጋቸውን ለመግለጽ እንዴት እንደሚችሉ ለማሳየት ይረዳል።

"ዛሬ ትምህርት ቤት ጥሩ ቀን እንደዋልክ ተስፋ ኣደርጋለሁ። ባቅፍህ ደስ ይለኛል ካልፈለግክ ግን የእጅ ሰላምታ ብቻ መለዋወጥ እንችላለን። እንዴት ብለህ ልትሰናበተኝ ተፈልጋለህ?"

"ያዘነ ይመስላል። ማታቀፍ እንደሚፈልግ እና እንደማይፈልግ ልትጠይቂው/ቀው ትችያለሽ/ላለህ ወይም ሓዘኑን/ሓዘኗ እንድትረሳ/እንዲረሳ ምን ማድረግ ትችላለህ/ያለሽ?"

ልጆችን ኣይሆንም ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና የሌሎችን ስሜት እንደት መረዳት እንደሚችሉ ማስተማር።

"ድመቷ ጀርባዋን መታሸት ትወዳለች። ሆኖም ግን ከሄደች ወይም ጆሮዋን ወደኋላ ካደረገች ኣልወደደችውም ማለት ነው። ስለዚህ ማቆም ኣለብህ።"

"ከሱ ጋር ሲላፉ ፊቱን ይዩት። የወደደው እና መቀጠል የሚፈልግ ይመስላል?  ፈገግ እያለ ወይም እየሳቀ ነው ወይ?  ጫዋታውን ለኣጭር ግዜ ሲያቆሙ፤ ጨዋታውን መቀጠል ይፈልጋል ወይ?"

ከሌሎች የቤተሰብ ደህንነት እቅዶች ጋር የሰውነት ደህንነት እቅድ መመሪያዎችን ያጠቃሉ።

"የሌሎች ሰዎች ሓፍረተ ስጋ መንካት ወይም ለሌሎች ሰዎች ሃፍረተ ስጋህን ማሳየት ኣግባብ ኣይደለም። ምክንያቱ እነዚህ የሰውነት ኣካላት የግል ናቸው እና። ሌሎች ሰዎችም እነዚህ ሕጎች ማክበር ኣለባቸው።"

"ኣንዳንድ ግዜ የሆነ ነገር ደስ የማይልህ ነገረ ካለ ወይም ውስጥህ ከነገረህ ቦታውን ለቀህ መሔድ ጥሩ ነው።"

ውይይቱን ለጆች ሪፖርት እንዲያደርጉ ክፍት ይተዉት።

"የሆነ ሰው የግል ህፍረትህን ከነካህ ወይም የቤታችንን ሕጎች ካፈረሰ ለኔ ወይም ለሌላ [የምታምነው ሰው] ስለዚህ ጉዳይ ማናገር ትችላለህ። ምንም ችግር ኣያጋጥምህም።"

"የኔ ሓላፊነት የኣንተን ደህንነት ማረጋገጥ እና ይህን በተመለከተ ኣንተን መረዳት ነው። ስለዚህ የሆነ ሰው ስሜትህን ከጎዳ፣ ካስቆጥህ፣ እንድታዝን ካደረገህ፣ ካደናገረህ ወይ ሰላም ከነሳህ ሁሌም ለኔ ልትነግረኝ ይገባል።"

ለልጅህ ምን እያስተማርክ እንደሆነ ለሌሎች ንገር። ይህን መረጃ ሌሎች ወላጆች፣ የልጅህ ኣስተማሪዎች፣ የደይኬር ኣገልግሎት ሰጪዎች፣ ሞግዚቶች፣ ኣያቶች እና ቤተሰቦች (ዘመዶች) ንገር።

"ልጃችንን ስለመፍቀድ ለማስተማር እየሞከርን ነው። ሰውነቷ/ቱን እንዴት ለሌሎች መቅረብ እንዳለበት ምርጫ እንዳለው እንዲማር ስለምንፈልግ እባካችሁ ከማቀፋችሁ ወይ ከመሳማችሁ በፊት ፍቃድ ጠይቁት/ቋት። ያለፍላጎትዋ የሆነን ሰው እንድታቅፍ ወይም እንድትስም ኣናስገድዳትም።"

"እራስን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ የደህንነት ሕጎች እያስተማርነው ነው። የሆነ ሰው ካስቸገረው ወይም የሆነ ነገር ሰላም ከነሳው እንዲነግረን ነግረነዋል።"

# ...መፍቀድን፣ የሰውነት ክልል ማስከበር እና መንካት ማስተማር

ልጆች ከቤት ውጪ ሰዎች እንዴት ሂወትን መኖር ወይ እርስ በርስ መገናኘት እንዳለባቸው ኣስተሳሰባቸውን የሚቀይር ብዙ ነገር ይሰማሉ። እንዳንድ የሚሰሟቸው ነገሮች መጥፎ ናቸው። እነዚህ ልጆች ሌሎችን በመጥፎ ሁኔት እንዲቀርቡ ያደርጋል። ከባልንጀሮቻቸው ወይም ከቴሌቪዥን ስለሚሰሙት ነገር ልታናግሯቸው ይገባል። ጾታ ላይ የተመሰረተ የሂወት ተራ እና የልጆች ኣቅመቢስነት የሚሉ ኣስተሳሰባቸውን መፈተን ትችላላችሁ። የወጣቶች እና ኣዋቂዎች ወሲብን የሚመለከቱ ኣስተያየቶችን ልጆች ባይሰሟቸው ይመረጣል። ልጆች የሆነ ወሲባዊ ይዘት ያለው የቴሌቭዥን ፕሮግራም ወይም ፊልም ማየት የለባቸውም።

ሁሌም ወንዶች እና ሴቶችን በኣንድ ዓይነት መመሪያ እና እኩል ተስፋ ማየት ያስፈልጋል። ስለወንዶች የሚነገሩ ኣንዳንድ ጎጂ መልእክቶች ለምሳሌ ሓይለኛ መሆን ኣለባቸው፣ ሓላፊዎች እና ስሜታቸውን ኣያሳዩም የሚሉ። ስለሴቶች የሚነገሩ ኣንዳንድ ጎጂ መልእክቶች ለምሳሌ ደካሞች ናቸው፣ በቀላሉ ይባባሉ እና መልካቸው በጣም ኣስፈላጊ ነው የሚሉ ይገኙበታትል። እንደዚህ ያለ እምነት ባላቸው ሕብረተሰቦች መሃከል ወሲባዊ በደል የማጋጠም ብዙ ግዜ ሰፊ እድል ኣለ።

## ወንዶች...

- ሊያዝኑ
- ስለ ለሌሎች ስሜት ሊያስቡ
- ስለ ጉዳዮች መነጋገር
- ለሌሎች ማሰብ
- ትሑት መሆን
- ጥሩ ጓደኛ መሆን
- ደስ ባላቸው መጫወቻ መጫወት ይችላሉ

ሁሉም ልጆች እነዚህን ነገሮች ሊያደርጉ ይችላሉ!

## ሴቶች...

- ሊናቆሩ
- ሊቆጡ
- ሓይለኛ መሆን
- ሰዎችን ማዳን
- መሪዎች መሆን
- ሕግ ማውጣት
- ደስ ባላቸው መጫወቻ መጫወት ይችላሉ

ወላጆች ለልጆቻቸው ከነሱ የሚጠብቁትን ነገር የማሳወቅ እና መመሪያ የማውጣት መብት ኣላቸው። ልጆች **ኣንዳንድ ግዜ ኣይሆንም ማለት እና ሃሳባቸው እንዲያሰሙ መብት እንዳላቸው ማወቃቸው** ኣስፈላጊ ነው። ይህ ከመበደል ሊከላከልላቸው ይችላል። በዳይ ሁልግዜ ለኣዋቂዎች ወይም በዕድሜ ለሚበልጧቸው ኣይሆም ማለት የምይችሉ ልጆችን ያጠቃሉ። እርስዎ ያወጡትን ሕግ እያከበሩ እና ተግባር ላይ እያዋሉ የልጆችዎን ኣስተያየት እንደሚያከብሩ በምሳሌነት ማሳየት ይችላሉ። ልጅዎ እንዳንድ ግዜ ከርስዎ ጋር በሃሳብ እንዲለያይ እና ኣይሆንም ማለት እና ራሱ ለራሱ እንዲወስን እድል ስጡት። ልጅዎ ደስ የማይል ነገር ካየ መቃወም መቻሉ ኣስፈላጊ ነው።

“ተሳስቻለሁ ይቅርታ! ኣንደሚያሳፍርህ ኣላወቅኹም። እንዴት እንደሚሰማህ ስለነገርከኝ ኣመሰግናለሁ።”

“የምትለውን ነገር ኣከብራለሁ፤ ስለዚህ እኔ ኣቁሜኣለሁ ምክንያቱም ኣንተ ስለጠየቅከኝ።”

“ደስ በማይልህ ሁኔታ የሆነ ሰው ከነካህ ምን ማድረግ ትችላለህ? ከሕግ ውጪ የሆነ ነገር እንድታደርግ የሆነ ሰው ከጠየቀህ ምን ታደርጋለህ?”

# ...ሕብረተሰቡ የሚያስተላልፈውን መልእክት መግጠም

ስለእነዚህ ኣርእስቶች መነጋገር የመከላከል ኣንዱ ኣካል ነው። ሌላው ኣስፈላጊ የመከላከል ኣካል **ወጣቶች እና ኣዋቂዎች የሚያሳዩዋቸው ኣሳሳቢ ባህሪያት** መከታተል ነው። ሁልግዜ ልጅዎ የት እንዳለ፣ ከነማን ጋር እንደሆነ እና ማን ከነሱ ጋር እንዳለ ማወቅ ኣስፈላጊ ነው። ትልቅ ሕጻናት በእድሜ ከነሱ ያነሱ ሕጻናትን ረዘም ላለ ግዜ ያለ ቁጥጥር እንዲጠብቋቸው ኣታድርጉ። **በደል የሚፈጸመው ልጁ በሚያውቀው ሰው ነው።** ኣብዛኛውን ግዜ በሚስጢ ነው የሚፈጸመው። ልጆች በሌሎች ልጆች እና ኣዋቂዎች ማለት ኣብረው ኣንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ወይም የወጣቶች ፕሮግራም ላይ የሚሰሩ ሰዎች በደል ሊደርስባቸው ይችላል። ኣንድ ሰው ደስ ካላልዎ ሁሌም **ውስጥዎን ይመኑ፤** በፍጹም ልጅዎ ከነዚህ ሰዎች ጋር ግዜ እንዲያሳልፍ መፍቀድ የለብዎትም። በዳዮች ሁሌም ትሁት እና ቅኑ መስለው ይቀርባሉ ምክንያቱም ከልጅዎ ጋር የጠበቀ እና እምነት ላይ የተመሰረተ ጓደኝነት መመስረት ስለሚፈልጉ።

## ኣዋቂዎች ላይ የሚታዩ ኣሳሳቢ የባህሪ ለውጦች ምሳሌዎች፡

- **የቦታ ማጥፋት** : ለልጅ ልዩ ፍቅር እና ብዙ ማበረታቻ ቃላት መስጠት (ወይም ኣንስተኛ የልጆች ቢድን)።
- **ልዩ ሕክምና:** ለልጅ ልዩ ስጦታ መስጠት እና ልዩ መብት መስጠት ወይም ሕግ እንዲጥሱ መፍቀድ።
- **ልጆች ላይ ያተኮረ:** እየተጫወቱ እያሉ ደጋግሞ መንካት፣ ከኣዋቂዎች ጋር ይበልጥ ከልጆች ጋር የተሻለ ወዳጅነት መመስረት፣ ከልጆች ጋር ከወላጆች ጋር ወይም መጉዚቶች ሳያማክሩ ዝምድና መመስረት
- **ክልልን ኣለማወቅ:** ልጁ ደስተኛ ባይሆንም ወይም እንዲያቆሙ ቢጠይቅም ኣለማቋረጥ፣ ስለ ጾታዊ ነገሮች ወይም የግል ጉዳይ ደጋግሞ መናገር
- **ምስጢር:** ልጆችን ምስጢር እንዲጠብቁ መጠየቅ፣ ከልጁ ጋር ብቻ ለመሆን ቦታ እና እጋጣሚ መፈለግ

## ከልጆች ጋር ኣሳሳቢ ባህሪያት ያሚያሳይ እና ወሰኑን የማያውቅ ሰው እንዴት ብሎ ማናገር ይቻላል:

- "ጨወታው የሰለቸው ይመስላል።"
- "ልጆችን ስለ __________ ስትናገራቸው ደስ ኣላለኝም።"
- "እባክህ ከልጆቹ ጋር ስትጫወቱ በሩን ክፈቱት። እንተ ብትኖርም እንኳን ልጆቹን ሲጫወቱ ማየት እፈልጋለሁ።"
- "ስለ ልጆቹ ኣካል ስትናገር እና ይህን 'ለጨዋታ' ነው ያልከው ደስ ኣላለኝም።"

ወሲባዊ በደል ከመከላከያዎች ኣንዱ **የሚያሳስብ ባህሪያት ስታዩ ወዲያው መቃወም እና ስለጉዳዩ መናገር** ነው። ልጆቻችሁ ይህን ስታደርጉ ካዩዋችሁ ጥሩ ምሳሌ ነው። ብዙ ሰዎች ነገሩ ገብቶዋቸው ኣሳሳቢውን ባህሪያት ወዲያው ሊያቆሙት ይችላሉ። ባንጻሩ በዳይ ከሆነ እራሱን ለመከለከል ይሞክራል ወይም የማያሳስብ ጉዳይ እያሳሰበህ ነው ይልሳ። ብትናገሯቸው ኣይሰሙም ወይም በይበልጥ ሚስጢረኛ ይሆናሉ። እንደዚህ ካጋጠመ ይህ ሰው ልጆች ኣካባቢ በሚሆንበት ግዜ ልብ ብለው ይታዘቡ። ለባንጀራዎ ወይም ለቤተሰብ ኣባላት ይጠቁሙ። ለምክር ወደ ማእከላችን (ወይም ባካባቢዎ ወደሚገኝ የወሲባዊ በደል ፕሮግራም) ደውሉ።

እሁኑኑ መጀመር ትችላላችሁ። ልጆቻችሁ ጥያቄ ወይም የሚያሳስባቸው ነገር ካለ ምንም ያህል ትንሽ ይሁን ተገቢ መልስ በመስጠት ሁሌም ከጎናቸው እዳላችሁ ኣሳይዋቸው። ይስሟቸው ያዳምጧቸው። ልጆቻችሁ ጥያቄ ወይም የሚያሳስባቸውን ነገር ስነግሯችሁ፤ መጀመሪያ ስለነገሯችሁ በጣም ደስተኛ መሆናችሁ ንገሯቸው። ዛሬ ትንሽ ጥያቄ ይዘው ሲመጡ በደስታ ከተቀበሏቸው ሌላ ቀን ከበድ ያለ ጥያቄ ካላቸው ወደርስዎ ይዘው ለመምጣት ኣይቸገሩም።

ምንም ያህል ጉዳዩን ለማስቀየር ብንሞክርም፤ ወሲባዊ በደል ኣሁንም ቢሆን ሊያጋጥም ይችላል። የርስዎ መልስ እና ድጋፍ በጣም ኣስፈላጊ ነው። ልጆች ወሲባዊ በደል ከሚያደስው ተጽኖ ሊፈወሱ እና መፈወስ ይችላሉ። ለእርስዎ እና ለልጅዎ እርዳታ ኣለ።

▶ ልጅዎ ወሲባዊ በደል ወርዶበታል ብለው ከጠረጠሩ ግን እርግጠኛ ካልሆኑ በቅርብ ይከታተሏቸው። የስሜት ለውጥ ካላቸው ይከታተሉ። ውይይታችሁን ነጻ የሆነ ጥያቄ በመጠየቅ ለምሳሌ፡“የሆነ ነገረ የሚያስጨንቅሽ ወይም ሚያስቸግርሽ  ነገር ካል ሁሌም ልታናግሪኝ ትችያለሽ።”  ተጨማሪ ምክር ለማግኘት ወደኛ (ወይም ወደ ባካባቢያችሁ ያለ የወሲባዊ በደል መከላከል ፕሮግራም) ደውሉ።

▶ ልጅዎ ወሲብን በሚያመላክት ኣግባብ ተነክቻለሁ ወይም ወሲባዊ በደል ደርሶብኛል ካለችዎ፣ መጀመሪያ መናደድ እና ጉዳዩን ለማመን መቸገር የተለመደ ነው። በዚህ ግዜ ግን እራስዎን ማረጋጋት እና ልጅዎ የትለውን ነገር ማመን ያስፈልጋል። ይህ መናገራቸው ጥሩ መሆኑን ልትነግሯቸው ይገባል።

▶ ወሲባዊ በደል ሪፖርት ከተደረገ ልጁን ያለ ክትትል ከበዳዩ ጋር መቀራረብ የለበትም። ባቅራቢያችሁ ወዳለ የፖሊስ ጣቢያ ወይም ቻይል ፕሮተክሽን ሰርቪ ሪፖርት ልታደርጉ ይገባል። የልጅዎን ደህንነት ለማረጋገጥ እና ናሙና ለመሰብሰብ የህክምና ምርመራ ማድርግ ተገቢ ነው። እርዳታ ለማግኘት ወደኛ መደወል ትችላላችሁ።

▶ ልጅዎ ወሲባዊ ተግባራትን እያሳየች ወይም ሌሎችን ተገቢ ባልሆነ መንገድ እየነካች ነው ብለው ካሰቡ ባለሙያ ልታማክሩ ይገባል። ስለ የሰውነት ድህነት ሕጎችን ከልጅዎ ጋር መነጋገር እና ምን ኣይነት መንካት ተገቢ ነው ምን ዓይነት መንካት ተገቢ ኣይደለም ሊነግሯቸው ይገባል። እነዚህ ሕጎች እንደ ሌሎቹ ስነስርዓት እና ደህንነትን የሚመለከቱ ሕጎች ጠበቅ ኣድርገው ሊያስተምሩ እና መተግበራቸው ሊከታተሉ ይገባል። ተጨማሪ ምክር ለማግኘት ወደኛ (ወይም ወደ ባካባቢያችሁ ያለ የወሲባዊ በደል መከላከል ፕሮግራም) ደውሉ።

## ተጨማሪ መረጃዎች:

- የዋሽንግተን የወሲባዊ ጥቃት ፕሮግራም (ሴክሽዋል ኣሷልት ፕሮግራም) ሕብረት: **www.wcsap.org**
- ብሔራዊ የልጆች ትራውማቲክ ስትረስ ኔትዎርክ (ናሽናል ቻይልድ ትራውማቲክ ስትረስ ኔትዎርክ): **www.nctsn.org**
- ለበለጠ መረጃ ድሕረገጻችንን **www.hcsats.org**. ይጎብኙ። “Resources” የሚለውን ሊንክ ይጫኑ።


የሃርቨርቪው ሴንተር ፎር ሴክሹዋል ኣሷልት ኤንድ ትራውማቲክ ስትረስ
ጽ/ቤቶች በሲያትል፣ ሬድመንድ፣ ቬልቪው እና ሾርላይን
የምንሰጠው ኣገልግሎት: የህክምና ምርመራ፣ የችግር ግዜ እርዳታ እና የምክር ኣገልግሎት

**www.hcsats.org**
**206-744-1600**



UW Medicine
HARBORVIEW MEDICAL CENTER

ይህ ፕሮጀክት በሲያትል ችልድረንስ እና ሞልተኒ ፋሚሊ እንደውመንት የተደገፈ ነው
Seattle Children's
HOSPITAL · RESEARCH · FOUNDATION


**...ህጻናት ወሲባዊ በደል ሲደርስባቸው ካዩ እርምጃ ይውሰዱ**